ግብርና ሚኒስቴር

በእንስሳት ሀብት ዘርፍ

የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት

# የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት

ሐምሌ **2012** ዓ.ም

በግብርና ሚኒስቴር

በእንስሳት ሀብት ዘርፍ

# የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት
# የ **2012** በጀት የሶስተኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት

ደርሞ

በሚኒስቴር መ/ቤታችን ሥር ከተዋቀሩት ዳይሬክቶሬቶች አንዱ የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት ሲሆን ይህ ዳይሬክቶሬት በዋንኛነት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚገነቡትን የኤክስፖርት ቄራዎች ከግንባታ ቦታ መረጣ ጀምሮ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ቄራዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በማገዝ በመጨረሻም ግንባታቸው ሲያልቅም የሙከራ ዕርድ በማካሄድና በመፈተሽ የዕውቅና ሰርተፊኬት ይሰጣል።

በመቀጠልም ቄራዎቹ የተቀባይ አገሮችን የቅበላ መስፈርት እንዲያሟሉ ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ምርታቸውን የመላክያ ፈቃድ እንዲያገኙ ከሚመከታቸው አካላት ጋር ይሠራል። የመላኪያ ፈቃድ ላገኙ ኤክስፖርት ቄራዎች የስጋ ምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ ዓለም ዓቀፉን አሰራር እና የተቀባይ አገሮችን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ የኢንስፔክሽን እና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት በመስጠት የኤክስፖርትሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርትን ሰርቲፋይ በማድረግ ወጪ ንግዱ እንዲቀጥል ተገቢውን ዋና ድርሻ ይጫወታል።

በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎችና ከተሞች ለሚገኙና ወደ ውጪ ሀገር ምርታቸውን ለመላክ ፈቃድ ላገኙ 10 ኤክስፖርት ቄራዎች ይህ አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪም የእንስሳትን ተረፈ ምርት በማቀነባበር ወደ ውጪ ለሚልኩ 8 ባለሀብቶች ተመሳሳይ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል።

በዋና መ/ቤት ደረጃ ዳይሬክቶሬቱ በአብዛኛው በየቄራው የሚሰራውን የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን ሥራዎች የማስተባበር፣ በየደረጃው ያለውን የእውቀት፣ የክህሎትና የግብዓት ክፍተት በመለየት የመሙላት ተልዕኮ ያዘለ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ አገሮችን የሥጋና የተረፈ ሥጋ የመቀበያ መስፈርት በመገምገምና የምርቱን ተቀባይነት ለማግኘት የሚያስችል መስፈርት የማሟላት ሥራ ወደ ኃላ በጋራ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የወጪ ንግድን የመጨመር ሥራን አካቶ ይሠራል። በተጨማሪም የሥጋና የተረፈ ሥጋ ኤክስፖርት ጥራትና ደህንነትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት የሚሰራ ሲሆን በመዳረሻ አገራት ችግርም ሲያጋጥም ከየአገራቱ ከተቆጣጣሪ አካላት ጋር በቅርብ በመገናኘት መፍትሄ ይሰጣል።

እንደሚታወቀው በዚህ ዓመት ወር በዳሬክቶሬታችን በዋነኝነት ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መስጠት ሲሆን በዘህም መሰረት በሁሉም ኤክ/ቄራዎች ለ 4,134,000 እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ፣ ለ 4,130,000 እንሰሳት ላይ የድህረ ዕርድ ምርመራ በማካሄድ 43,000 ቶን ስጋ እና ተረፈ ስጋ ወደ ውጪ እንዲላክ 8,000 ዓለም አቀፍ የሥጋ ጤናማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 1,856,241 (44.9 በመቶ) እንሰሳት ላይ የቅድመ ዕርድ ምርመራ፣ 1799324 (43.6 በመቶ) እንሰሳት ላይ የድህረ ዕርድ ምርመራ የተካሄደ ሲሆን ከነዚህ ከታረዱ እንሰሳት ላይ 14,273 ቶን (33.2 በመቶ) ሥጋና ተረፈ ሥጋ በማምረት 8,150 (101.9 በመቶ) ዓለም አቀፍ የሥጋ ጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት የሥጋ ምርቱ ወደ ውጪ እንዲላክ የድርሻውን ተወጥቷል። በዚህም መሰረት ለዕርድ ከቀረቡት እንሰሳት የኤክስፖርት መስፈርቱን የሚያሟሉትንና በህጉ መሰረት የቀረቡትን ሁሉንም እንሰሳት (መቶ በመቶ) የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት በመስጠት የሥጋ ምርቱን ለመላክ ተችሏል።

የዚህ ዓመቱ ሥጋና ተረፈ ስጋ ኤክስፖርት ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 4,358.93. ቶን ስጋ ቅናሽ ያሳየ ቢሆንም 243.28 ቶን ተረፈ ስጋ ግን ጭማሪ ያሳየ መሆኑን ለመገምገም ተችሏል። ለዚህም በከፍተኛ ደረጃ ሥጋ ኤክስፖርት መቀነስ ምክንያቶቹ የኤክስፖርት መስፈርቱን የሚያሟሉ እንሰሳት በሚፈለገው መጠን በገበያ ያለማግኘት፣ የእንሰሳት ገበያው በደላሎች የተሞላና እና የገበያ ሰንሰለት በመርዘሙ ምክንያት አላስፈላጊ ዋጋ መቆለል፣

እንሰሳት በኮንትሮባንድ መልክ በስፋት አሁንም እየወጡ በመሆኑና 6 ቄራዎች ማለትም ሐሺም፣ አበርገሌ፣ ደ/ዘይት ኤልፎራ፣ አክሸከር እና ፍሪጎሪፊኮ ቦራን ፉድ ኤክ/ቄራዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ማቆማቸው የሚጠቀሱ ቢሆንም በተለይም በዚህ ወቅት ከኮቪድ በሽታ ጋር ተያይዞ የእንሰሳት አርቦት ላይ ጫና በመፈጠሩ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የኤክ/ቄራዎች አጠቃላይ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማነስ እንዲሁም በገበያ የሚመራ የምርምርና ዕድገት አሰራር ሥርዓት አለመኖር ጋር ተያይዞ ቄራዎቹ ሲቋቋም ከነበራቸው የዕርድ አቅም (Designed Slaughtering Capacity) በታች ማከናወን ይጠቀሳሉ።

እንደ ምክረ ሀሳብ የእንሰሳት ዕጥረትን ለመቅረፍ ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የሚቀረፍበትን የተለያዩ አማራጮችን መተገበር ሲሆን በሌላው ጎን ግን መንግስት በቁርጠኝነት የእንሰሳት ኮንትሮባንድን በጋራ የሚከላከልበትን ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ እንደ አገር ይገባል። በሚ/ር መ/ቤት ደረጃ ሥራ ያቆሙ ቄራዎችን በቅርበት ችግራቸውን በመፈተሽ፣ በማገዝና በማብቃት ሥራ የሚጀምሩበት ሁኔታን ማመቻቸት የሚያስፈልግ ሲሆን በዚህም ረገድ የአበርገሌ ኤክ/ቄራን በቅርብ በመፈተሽ የማስስተካከያ ግብረ መልስና በሚ/ር መ/ቤታችን ዕውቅና የተሰጠውና አክስፖርት እንዲደርግ ድጋፍ በመስጠት ላይ እንገኛለን፣ የጅግጅጋ እና የሐሺምን አክ/ቄራዎችንም በተመሳሳይ ኤክስፖርት እንዲጀምሩ ከየቄራው ማናጅመንት ጋር በቅርበት በመስራት ላይ የምንገኝ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ቄራውን በመፈተሽ እና ማስተካከያ ስራዎችን በመስራት የ2020 እ.ኤ.አ ዕውቅና ሰርተፊኬት በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል።

በዋነኝነት የዳይሬክቶሬታችን ሥራ በሥርዓት ላይ የተመሰረተ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት የመገንባት እንቅስቃሴ ሲሆን በዚህ ግማሽ ዓመትም ሁሉንም በስራ ላይ ያሉ ኤክስፖርት ቄራዎችን በሚኒስትር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ስታንዳርድ የአሰራር ሥርዓት (SOP) እና በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000) ሥርዓት መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ለማድረግ ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን ሁሉም ቄራዎች በክትትሉ ግዜ የተገኙትን ክፍተቶች እንዲያርሙ ግብረ መልስ ተሰጥቷል።

መግቢያ

የዳይሬክቶሬቱ ቢ ኤስ ሲ ዕቅድ የ2ኛውን የዕ ት ዕ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀና ከሚመከታቸው ባለሞያዎች ጋር በውይይት የዳበረ ሲሆን ይህንንም ዕቅድ ከዘርፉ ማናጅመነት ጋር በማዳበር የመጨረሻ ዕቅድ በማድረግ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም ረገድ ይህንን 2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አስከፈጻሚ የዋናው መ/ቤት ባለሞያዎችና በየቄራው ለሚገኙ ፈጻሚዎች አውርዶ ካስኬድ በማድረግ እንዲሁም በመፈራረም ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ክንውኑን በየሳምንቱ በሞባይል የአጭር ጽሁፍ መልዕክት በመቀበልና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በሰልክና በአካል የመነጋገርና የመወያየት ሁኔታ የነበረ ሲሆን በየወሩ ሪፖርቱን በመገምገም ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል።

ከዚህም በተጨማሪ የፕሮጀክት ሥራዎች ጎልተው እንዲታቀዱና የትራንስፎርሚሽን አጀንዳ ሥራዎች በተለይም ከግብርና ትራንስፎርኔሽን ኤጀንሲ ጋር በጋራ የሚሰሩ ካሉ በዕቅድ ውስጥ እንዲገቡና እንዲከናወኑ ለማድረግ ተሞክሯል። ከዚህም ሌላ በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ለወጣቶችና ሴቶች ሥራ ፈጠራ ዕድል፣ ለልዩ ድጋፍ ለሚሹ አርብቶ አደር ክልሎችና አካባቢዎችም ጭምር የሚከናወኑ ሥራዎች በዕቅድ ውስጥ ለማካተትና ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል ለማየትና የተቻለውን ያህል በማካተት ለመስራት ተሞክሯል።

በተጨማሪም የኮቪድ 19 አደጋን ለመቋቋም እንደ ግብርና የአጭርና መካከለኛ ግዜ ዕቅድ በማውጣትና ከዋነኛው ሥራችን ጋር በማጣጣም የተሰራበት ሁኔታ እንዳለ እና በዚህም ረገድ የሰራተኞችን እና የሥጋ የምርቱን ደህንነት በመጠበቅ በኩል የተቻለውን ጥረት በማድረግ እንዲሁም ኤክስፖርቱ እንዳይስተጓጎል በማድረግ ከስጋ ኤክስፖርቱ የሚገኘውን የውጪ ምንዛሪ ለማስጠበቅ ተችሏል።

የዓበይት ተግባር አፈጻጸም

ዕይታ፣ ሕብረተሰባዊ/አገራዊ

ግብ **1.** የተገልጋይን የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አሁን ካለበት **80** በመቶ ወደ **90** ማሳደግ፣

- በዓመቱ 2 የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ተከናውኗል።

- በዓመቱ ይህንን ጥናት በመተንነን ዕርካታን ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ዕርካታው 90 በመቶ የደረሰ መሆኑ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን አንዳንድ ቄራዎች ለምሳሌ እንደ ሀላልና ሞጆ ሞደርን ቄራዎች በተለይም ከእንሰሳት አቅርቦትና ገበያን ከማስፋት አኳያ ግብርና ሚኒስቴር/ዳይሬክቶሬቱ የሚፈለገውን ያህል ክትትልና ዕገዛ አላደረገልንም፣ ችግራችንን ለመፍታት ረገድ ቸለልተኛ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው።

ግብ **2.** የኤክስፖርት ቄራ የዕርድ መስመር ሰራተኞችንና የቦሌ ስጋ አውራጅ-ጫን ሰራተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

- በዓመቱ በተለያዩ ኤክስፖርት ቄራዎች ለሚገኙ 1000 የዕርድ መስመር ሠራተኞች ስለ ዘመናዊ የእንሰሳት አስተራረድና አገፋፈፍ ሥርዓትና ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተሃድሶ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1250 (929 ወንዶች እና 321 ሴቶች) ሰራተኞችን በተለይም በሉና፣ በሞጆ ሞደርን፣ በደ/ዘይት ኤልፎራ፣ በሃላል፣ በአልኑጁም እና በመታህራ ኤልፎራ ኤክ/ቄራዎች የግማሽ ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ዕቅዱን 125 በመቶ ያከናወነ ሲሆን ይህ ክንውን ከባለፈው ዓመት ተመሳሰይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር በ 99 ሰልጣኝ ከፍ ያለ ነው።
- በዓመቱ ቦሌ አየር መንገድ ፍረሽ ፓርት ለሚገኙ 50 ስጋ አውራጅ-ጫን ሰራተኞች ሥለ ሥጋ አያያዝና ደህንነት እንዲሁም የግል ንጽህና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 30 ሰራተኞችን (25 ወንዶችና 5 ሴቶች) ከቦሌ ኳራንቲን ጋር በመተባበር በማሰልጠን የዕቅዱን 60 በመቶ ለማከናወን ተችሏል። ዕቅዱ ያነሰበት ምክንያት በዚህ በግንቦት ወር መጨረሻ ሰራተኞችን ለማሰልጠን በዕቅድ ቢያዝም በኮቪድ 19 ችግር ምክንያት ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም።

ግብ **4.** ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መስጠት፣

- በዓመቱ 4🌶□◀ ▶🌶000 እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1🌶856🌶241 (44.9 በመቶ እንሰሳት ለመመርመር ተችሏል፣ ከዚህ በተጨማሪም ለሉና እና ለአበርገሌ ኤክ/ቄራዎች ለሀገር ውስጥ አቅርቦት 3🌶450 ዳልጋ ከብትና 435 በግና ፍየል እንሰሳት የምርመራ አገልግሎት አግኝተዋል። አጠቃላይ የቅድመ ዕርድ ምርመራ ክንውኑ ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 340🌶819 የቀነሰ እንደሆነ ተገምግሟል።
- በዓመቱ 4🌶□30🌶000 እንሰሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1🌶799🌶324 (43.6 በመቶ) እንሰሳት መመርመር ተችሏል፣ ከዚህ ከተመረመሩት እንሰሳት ውስጥ 3🌶450 ዳልጋ ከብትና 435 በግና ፍየል በሉና እና በአበርገሌ ቄራዎች ለአገር ውስጥ ገበያ ለማዋል ታስቦ የተመረመሩ ናቸው። አጠቃላይ የድህረ ዕርድ ምርመራ ክንውን ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 284🌶306 የቀነሰ እንደሆነ ተገምግሟል።
- በዓመቱ 41🌶000 ቶን ሥጋና 2🌶000 ቶን ተረፈ ሥጋ ምርት ላይ ምርመራ በማድረግ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 12348 (30.1 በመቶ) ቶን ሥጋና 1925.96 (96.3 በመቶ) ቶን ተረፈ ሥጋ ላይ ምርመራውን በማካሄድ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፣ የዚህ ዓመቱ ሥጋና ተረፈ ስጋ ኤክስፖርት

ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 4358.93. ቶን ስጋ ቅናሽ ያሳየ ቢሆንም 243.28 ቶን ተረፈ ስጋ ግን ጭማሪ ያሳየ መሆኑን ለመገምገም ተችሏል።

- o ከላይ ከተጠቀሰው የሥጋ ኤክስፖርት በተጨማሪ 159.6 ቶን የበግና ፍየል ሥጋ እንዲሁም 481.4 ቶን የከብት ሥጋ በድምሩ 641 ቶን ስጋ በሉና እና በአበርገሌ ኤክ/ቄራዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተመርቶ በመቅረብ ተሽጧል።

- በዓመቱ 8000 የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለምርቱ ለመስጠት ታቅዶ 8150 (101.9 በመቶ) የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት ተግባር በማከናወን ኤክስፖርቱን ለመደገፍ ተችሏል። ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 594 ሰርተፊኬት የቀነሰ እንደሆነ ታውቋል።

የዚህ ዓመቱ ሥጋና ተረፈ ስጋ ኤክስፖርት ከዓምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነጻጸር 4358.93. ቶን ስጋ ቅናሽ ያሳየ ቢሆንም 243.28 ቶን ተረፈ ስጋ ግን ጭማሪ ያሳየ መሆኑን ለመገምገም ተችሏል። ለዚህም በከፍተኛ ደረጃ ሥጋ ኤክስፖርት መቀነስ ምክንያቶቹ የኤክስፖርት መስፈርቱን የሚያሟሉ እንሰሳት በሚፈለገው መጠን በገበያ ያለማግኘት፣ የእንሰሳት ገበያው በደላሎች የተሞላና እና የገበያ ሰንሰለት በመርዘሙ ምክንያት አላስፈላጊ ዋጋ መቆለል፣ አሁንም እንሰሳት በኮንትሮባንድ መልክ በስፋት እየወጡ በመሆኑና 6 ቄራዎች ማለትም ሐሺም፣ አበርገሌ፣ ደ/ዘይት ኤልፎራ፣ አክሽከር እና ፍሪጎሪፊክ ቦራን ፉድ ኤክ/ቄራዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ማቆማቸው የሚተቀሱ ቢሆንም በተለይም በዚህ ወቅት ከኮቪድ በሽታ ጋር ተያይዞ የእንሰሳት አርቦት ላይ ጫና በመፈጠሩ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የኤክ/ቄራዎች አጠቃላይ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማነስ እንዲሁም በገበያ የሚመራ የምርምርና ዕድገት አሰራር ሥርዓት አለመኖር ጋር ተያይዞ ቄራዎቹ ሲቋቋም ከነበራቸው የዕርድ አቅም (Designed Slaughtering Capacity) በታች ማከናወን ይጠቀሳሉ።

እንደ ምክረ ሀሳብ የእንሰሳት ዕጥረትን ለመቅረፍ ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የሚቀረፍበትን የተለያዩ አማራጮችን መተገበር ሲሆን በሌላው ጎን ግን መንግስት በቁርጠኝነት የእንሰሳት ኮንትሮባንድን በጋራ የሚከላከልበትን ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ እንደ አገር ይገባል። በሚ/ር መ/ቤት ደረጃ ሥራ ያቆሙ ቄራዎችን በቅርበት ችግራቸውን በመፈተሽ፣ በማገዝና በማብቃት ሥራ የሚጀምሩበት ሁኔታን ማመቻቸት የሚያስፈልግ ሲሆን በዚህም ረገድ የአበርገሌ ኤክ/ቄራን በቅርብ በመፈተሽ የማስተካከያ ግብረ መልስ የሰጠንና የደገፍን ሲሆን በተጨማሪም በሚ/ር መ/ቤታችን ቄራውን ዕውቅና የተሰጠውና አክስፖርት እንዲደርግ ድጋፍ በመስጠት ላይ እንገኛለን፣ የጅግጅጋ እና የሐሺምን አክ/ቄራዎችንም በተመሳሳይ ኤክስፖርት እንዲጀምሩ ከየቄራው ማናጅመንት ጋር በቅርበት በመስራት ላይ የምንገኝ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ቄራውን በመፈተሽ እና ማስተካከያ ስራዎችን በመስራት የ2020 እ.ኤ.አ ዕውቅና ሰርተፊኬት በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል።

ዕይታ፣ ሃብት

ግብ **8.** የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣

- በዓመቱ በመደበኛ የሚመደበዉን በጀትና አጠቃላይ ሀብት ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የአፈፃፀምና ሀብት አጠቃቀም ጥምርታ ማሻሻልና የበጀቱን 90 በመቶ ለመጠቀም ታቅዶ የበጀቱን 80 በመቶ ለመጠቀም ተችሏል።

ግብ **.** ግብ **9.** የሀብት ግኝትን ማሳደግ

- በዓመቱ ዓመት ሁሉም ኤክ/ቄራዎች ለተሰጣቸው አገልግሎት 2.5 ሚሊዮን ብር ክፍያ ወደ ሚ/ር መ/ቤታችን ባንክ አካውንት ገቢ እንዲያደርጉ ለማድረግ ታቅዶ 1.1985 (49.4) ብር ገቢ የተደረገ ሲሆን ክንውኑ ዝቅ ያለበት ምክንያት የአብዛኞቹ ቄራዎች ሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ክፍያ ባለማስገባታቸው ሲሆን (የሚጠየቁትም የወሩ ሪፖርት ከተጠቃለለ ቦሃላ በመሆኑ) በቀጣዩ ወር ይገባል ተብሎ ይጠበቃል።

- በዓመቱ1 ሀብት ሊያስገኝ የሚችል ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ቢታቀድም በስራ መደራረብ ምክንያት ሳይከናወን ቢቀርም በቀጣይ ሩብ ዓመት የሚከናወን ይሆናል።

ዕይታ፣ የውስጥ አሰራር፣

ግብ **10.** ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት፣

- በዓመቱ 1 ምርጥ ተሞክሮ ለመለየት፣ ለመቀመር እና ለማስፋፋት ታቅዶ እንደ ምርጥ ተሞክሮ የሚወሰድ እና የሚቀመር አሰራር ባለመገኘቱ አልተከናወነም።

ግብ **11.** ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ፣

- በዓመቱ የሳውዲ እና የዱባይ የኢንስፔክሽን ቡድንን በመጥራት 2 አዲስ ወደ ስራ የገቡ ቄራዎችን በማስገምገም ምርታቸውን እንዲልኩ ለማስቻል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የቤን ሮኢ ቄራን ዕውቅና በመስጠትና የተቀባይ አገሮች እንዲመጡ የግብዣ ደብዳቤ የተጻፈ ቢሆንም ምላሻቸውን ለማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፣ የኦጋኒክ ቄጥር 2 ቄራ 99 በመቶ ካለቀ ከ1 ዓመት በላይ ቢሆነውም ባለሀብቱ ሙሉ ለሙሉ ጨርሶ ዕውቅና እንዲሰጠው ምክር የሰጠን ሲሆን መልንሱም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።
- በዓመቱ ከእንሰሳት መድሃኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ጋር በመቀናጀት በስጋ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ጎጂ ቅሪትቶችን (Residues) በማመመርመር2 የላቦራቶሪ ውጤት ለማውጣትና ለሚመለከታቸው አካላት ለማሰራጨት ታቅዶ የተወሰነ ናሙና (እስከ 100) በመውሰድ እንደ ሙከራ የተሰራ ሲሆን ይህንን ስራ ግን ኦፊሺያሊ እንደውጤት ለማውጣትና ወደ ውጪ ለመላክ የራሱ የሆነ ውስንነት ሥላለው ለሚመለከታቸው ተቀባይ አገራት ለመላክ አልተቻለም፣ በመሆኑም ከላቦራቶሪው ማናጅመንት እና ከዘርፉ ጋር በመነጋገር ችግሩን በመለየትና መፍትሄ በማስቀመጥ የሚላክበት ሁኔታ እየተመካከርን የምንገኝ ሲሆን ከተባበሩት መንግስታቱ የምግብና እርሻ ድርጅት በተገኘ ድጋፍ የቅሪቶችን ምርመራ ዕቅድ ሰነድ (Residiue Monitoring Plan) ሥራ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህም መሰረት የዕቅዱን 25 በመቶ ለማከናወን ተችሏል።
- በዓመቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/፣ ከሥጋ አምራች ላኪዎች ማህበር፣ ከመ/ቤታችን የገበያና ግብይት ዘርፍ ወዘተ 4 ቅንጅታዊ ጥምረት በመፍጠር የሥጋ ምርመራና ኤክስፖርት ሥራዎችን ለማሳለጥ ታቅዶ 5 ተከናውኗል። በዚህም ከስጋ ላኪዎች ማህበር እና ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/ ጋር በመሆን ቄራ ሳይኖራቸው ያሉትን ኤክ/ቄራዎች በመከራየት የእርድ አገልግሎት በማግኘት ሥጋን ወደ ውጪ የሚልኩ ድርጅቶች/ግለሰቦች በእንሰሳት ግዢ ዋጋ እና በውጪ የመሸጫ ዋጋ ላይ ችግር በመፍጠራቸው ይህንን ችግር በመፍታት ኤክስፖርቱን ከጉዳት ለመጠበቅ እንዲቻል የመፍትሄ ውይይት በማካሄድ በዚህ በኩል ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦችና/ድርጅቶች ከቬርዴ ቢፍ በስተቀር እንዲታገዱ ለንግድ ሚኒስቴር ደብዳቤ እንዲጻፍ በመወሰንና በዚህም ውሳኔ ተመስርቶ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥጋ ምርመራና ሰርተፊኬሽን ሥራ እንዳይሰጥ ሰርኩላር በማስተላለፍ የሥጋ ኤክስፖርቱን ከአደጋ ለመታደግ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ከኦሮሚያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ጋር ስለ ሀላል አሰራርና አስፈላጊነቱ ላይ በተለይም የእኛ ከፍል ጋር በተያያዘ በየቄራዎች በመዘዋወር ግንዛቤ እንዲጨብጡና ስርዓቱን እንዲያስከብሩ የተደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከስጋና ወተት ኢንስቲትዩትና እና ከስጋ ማህበሩ ጋር በመሆን የእንሰሳት አቅርቦት ችግር የሚፈታበትን ሁኔታ ላይ በመመካከር እንዲሰራበት ተደርጓል።
- በዓመቱ የብሔራዊ የኤስ ፒ ኤስ ኮሚቴን ሥራዎችን በማስተባበር 16 ምክረ ሀሳብ ለበላይ ዓመራር ለማቅረብ ታቅዶ 2ቱ የተከናወነ ሲሆን በዚህም ረገድ ከፋኦ ጋር በመሆን እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በመገምገም

የቀረቡ ሲሆን የምንሰራባቸውን ጋይድላይኖች የመከለስና የማሳተም ስራው ከ16 ጋይድላይኖች 8 የመከለስ ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪዎቹም እተሰሩ የሚገኝ እንደሆነ እና በየቄራዎቹ የኤስ ፒ ኤስ ስራዎችን በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በሱፐርቪሽን መልክ የመገምገም ግብረ መልስ የመሰጠት ሥራ በማካሄድ የዕቅዱን በሙሉ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአገር አቀፉ የኤስ ፒ ኤስ ስትራተጂን በማጽደቅ ወደ ስራ ለማስገባት ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡

ግብ **12.** በሥርዓት ላይ የተመሰረተ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መገንባት፣

- በዓመቱ ኤክስፖርት ቄራዎች በሚኒስትር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ስታንዳርድ የአሰራር ሥርዓት (SOP) እና በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000) ሥርዓት መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ 4 ግዜ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ለማድረግ ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን በዚህም ረገድ አስሩም በስራ ላይ ያሉ ቄራዎች ላይ ድጋፍና ክትትሉ ተደርጎ የተገኘውንም ውጤት በግብረ-መልስ መልክ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት በተለይም የደ/ዘይት ኤልፎራና የሐሺም ቄራዎች አጠቃላይ እድሳት እንደሚያስፈልጋቸው የተነገረ ሲሆን የሐሺም ኤክ/ቄራ ይህንን በመቀበል ከፍተኛ የሆነ ዕድሳትና ጥገኛ በማድረግ በአሁኑ ሰዓት የጨረሰ ሲሆ፡ የደብረዘይት ኤልፎራም በተመሳሳይ የእድሳት ሥራ ተሰርቶ መስፈርቱን አሟልተው ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡ የመተሀራ ኤልፎራ ከቆሻሻ ፍሳሽ አወጋገድ ጋር ያለውን ችግር እንዲያስተካክል በተነገረው መሰረት አንድ ትልቅ ሴፕቲክ ታንክ ቁፋሮ በማስጀመር ችግሩን ለማቃለል ስራ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም ቀሪዎቹ ቄራዎች ያሉባቸውን አንዳንድ አነስተኛ ችግሮች በአስቸኳይ እንዲስተካከሉ ግብረ መልሱ ተሰጥቷቸው መስፈርታቸውን እኒዲያሟሉ ተደርጓል፡፡
- በዓመቱ በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000-2015) ወይም ሃሰፕ (HACCP) ሥርዓት በሶስተኛ አካል ዕውቅና ያገኙና በዳይሬክቶሬታችንም ተገምግመው ይሁንታን አግኝተው በትክክል በስርዓቱ መሰረት እየተገበሩ ያሉ 12 ቄራዎችን ይሁንታ ለመስጠት ታቅዶ 10 ቄራዎችን (ሉና፣ አልነጃም፣ ሞጆ ሞደርን፣ አቢሲኒያ፣ የመተሀራ ኤልፎራ፣ ኦርጋኒክ፣ ፍሳሪፊኮ ቦራን ፉድ፣ ደ/ዘይት ኤልፎራ፣ ጅግጅጋ፣ አበርገሌ፣ ሀላል እና ሐሺም) ኤክ/ ቄራዎችን በመፈተሽ የዕቅዱን (83.3 በመቶ) ለማከናወን የተቻለ ሲሆን ጅግጅጋ እና ሃሺም ቄራዎች ወቅቱን የጠበቀ ዕውቅና የሌላቸውና በሂደት ላይ ያሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በዓመቱ የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋው ስርዓት ላይ 2 የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት በማካሄድና መረጃን በመተንተን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ለማሰራጨት ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ በዚህም ረገድ ከኤርፖርት ቄራዎች በመኪና ተጓጉዞ ቦሌ የሚደርሰው የሥጋ የቅዝቃዜ መጠን በዓማካይ እስከ 3 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ለማውረድ የተቻለ ሲሆን ይህንን ወደ 2 ዲ/ሴግሬድ ለማውረድ እንዴት መስራት እንዳለብን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመኪኖቹን ማቀዝቀዣ መሳሪያን ካሊብሬት እንዲያስደረጉ፣ ከቄራ የስጋ ምርቱ ሲወጣ የካርካስ ቅዝቃዜው ከ 0 እስከ 1 ዲግሪ ሴ/ግሬድ መሆኑን ማረጋገጥ፣ መኪኖቹ በቀጥታ ወደ ቦሌ እንዲሄዱ እንዲደረግ (አላስፈላጊ መዘግየት እንዳይኖር ሲባል)፣ እንዲሁም ቦሌ ምርቱ ሲወርድ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግና በፍጥነት ወደ ማቀዝቀዣ ክፍል እንዲገባ መከታተልን የሚጠቀልል ስራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲሰሩ ተወስኖ ግብረ መልስ ተሰጥቶ ስራው ቀጥሏል፡፡

- በዓመቱ የአዳዲስ የኤክስፖርት ቄራዎች እና የሥጋ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ግንባታ ክንውን በመመሪያና ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ከቦታ መረጣ ጀምሮ 4 ግዜ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ በዚህም አራት በግንባታ ላይ ያሉ ቄራዎችን የተዳሰሱ ሲሆን አፈጻጸመቸውም ከ80 እስከ 99 በመቶ እንደሆነ የተገመተ ሲሆን በተለይም ኦርጋኒክ ቁጥር 2 ቄራ ግንባታው 99 በመቶ ከ 1 ዓመት ወር በፊት የደረሰ ቢሆንም አሁንም ድረስ ባለማለቁ ምክንያት ዕውቅና ለመስጠት አልተቻለም፡፡ የቬርዴ ቢፍ የከብት ቄራ

ዲዛይኑን በመከለስ እንደገና ስራ የጀመሩና በቀጣዩ ዓመት እንደሚያልቅ ከማናጅመንቱ ጋር በአካል በቦታው በመገኘት ለማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ስራው መጓተት የሚታይበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ወላይታ ከተማ መግቢያ ላይ ሊሰራ የታቀደውን የኤክ/ቄራ ቦታ የማጽደቅ ስራ የተሰራ ቢሆንም የቦታው ስፋት የማይበቃ በመሆኑ የከተማው ማዘጋጃ ቤት 1 ወይም ከዚያ በላይ ቦታ የሚጨምርለት ከሆነ መገንባት የሚቻል መሆኑን በደብዳቤ አሳውቀናል፡፡

- በዓመቱ የኤክስፖርት ቄራዎች የሚገኙትን 11 አነስተኛ ላቦራቶሪዎች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ 10 ( 90.1 በመቶ) ቄራዎች ላይ በማከናወን 5 ቄራዎች ማለትም ሉና፣ ሞጆ ሞደርን፣ አክሽከር፣ ፍ/ቦ/ፋ/፣ እና ደ/ዘይት ኤልፎራ በትክክል ያላቸውን ላቦራቶሪ እየተጠቀሙ የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹን ግን አልኑጁምና ሀላል የላቦራቶሪ ዕቃዎቹን እንዲያሟሉና መሰረታዊ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ማድረግ እንደሚገባቸው በማስረዳት ክትትልና ድጋፉ በቀጣይ እንደሚቀጥል የጋራ መግባባት ላይ ደርሰናል፡፡
- በዓመቱ አሁን እየላክን ካሉት አገራት በተጨማሪ አንድ አዲስ አገር ለመላክ የሚያስችል ስምምነት በማድረግ የወጪ ገበያን ለማስፋፋት ታቅዶ ከቻይና ከሚመለከተው አካል ጋር በተደረገ ውይይት ለግዜው መስፈርታቸውን ባለሟሟላታችን ማለትም ከድንበር ዘለል በሽታ መከላከልና ቁጥጥር መላላት ጋር ተያይዞ አሁንም ያልቻልን ሲሆን ለማላገርያ መንግስት ጋርም የተጀመረ ሥራ እንዳለ እና ሁለት ግዜ የእንሰሳት ጤና ሥርዓቱን የሚያብራራ ደብዳቤ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የላክንና መልሱን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጅቡቲ መንግስት ጋር የዶሮ ሙሉ ሥጋ መላክ የሚቻልበትን ሁኔታ ከአንድ ባለሀብት ጋር በመሆን የተሰራ ሲሆን በዚህም መሰረት ይህን ስጋ መላክ የሚያስችል ስምምነት የጅቡቲ መንግስት በቅርቡ በመስጠቱ ወደ አፈጻጸም ለመግባት በዝግጅት ላይ ብንገኝም የወቅቱ የኮቪድ 19 ችግር የባለሀብቱን ስራ ያጋተተው ቢሆንም በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አተባባሪነት ወደ ቻይና ገበያ ለመግባት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርቡ ተከታታይ የቨርቹዋል ውይይት ተጀምሮ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- በዓመቱ የጅግጅጋን ኤክ/ቄራን ያለበትን ችግር ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና በመፍታት ኤክስፖርት እንዲጀምር ለማድረግ ታቅዶ በዚህ ረገድ ከሚመለከታቸው የጅግጅጋ ቄራ ማናጅመንት እና ከስጋና ወተት ኢንስቲትዩት ጋር በመነጋገር የማሻሻያ ሥራዎችን ያስጀመርን ሲሆን በቅርቡም ወደ ጅግጅጋ በመሄድና ቄራውን ሱፐርቫይዝ በማድረግ የ 2020 ዓ.ም ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን በቅርቡ የኤክስፖርት ሥራውን ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ግብ **13.** የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽንን ማጎልበት፣

- በዓመቱ የኤክስፖርት ቄራዎችን 200 ሳምንታዊ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ለማቀናጀት ታቅዶ 191 (95.5 በመቶ) ሪፖርቶችን ተሰብስበው ተቀናጅተዋል፡፡
- በዚህ ዓመት የአንድ የኤክስፖርት ቄራ አገልግሎት ወርሃዊ የበሽታ ግኝት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ለማደራጀትና ለመተንተን እንዲሁም ለማሰራጨት ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ በዚህም መሰረት በሚከተለው ሠንጠረዥ የበሽታ ግኝቱን ለማየት ተሞክሯል፡፡

## Export Abattoir Case Analysis Report ( 56338 sheep and goat)

| S.N. | Diseas lists | Lung | Liver | Kidney | Heart | P.C | T.C |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Abscess | 172 (0.3%) | 104 (0.18%) | 2 (0.004%) | 4 (0.007%) | 51(0.09%) | 6 (0.01) |
| 2 | Jaundice | | 59 (0.10%) | | | | 10 (0.017%) |
| 3 | Bony | | | | | 32 (0.057%) | |
| 4 | Flukes | | 2641(4.69%) | | | | |
| 5 | Bruising | | | | | 253 (0.45%) | 10 (0.017%) |
| 6 | H. cyst | 298 (0.53%) | 31 (0.055%) | | | | |
| 7 | Calcified cyst | 131(0.23%) | 1527 (2.71%) | | | | |
| 8 | C. Tenucolis | | 3169 (5.62%) | | | | |
| 9 | Adhesion | 97 (0.17%) | 513 (0.91%) | | | | |
| 10 | S.hepatica | | 1585 (2.81%) | | | | |
| 11 | Pneumonia | 5104 (9.06%) | | | | | |
| 12 | Emphysema | 2681(4.76%) | | | | | |
| 13 | Nephritis | | | 90 (0.16%) | | | |
| 14 | Hepatitis | | 1198 (2.13%) | | | | |
| 15 | Cirrhosis | | 4015 (7.13%) | | | | |
| 17 | Pleuritis | | 0 | | | 135(0.24%) | |
| | **Total** | **8483** | **14842** | **92** | **4** | **481** | **16** |

- በዓመቱ ውስጥ 10 በሚ/ር መ/ቤታችን ዌብ ሳይት አስፈላጊ መረጃዎችን በመጫን ለተገልጋዩ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ ያሉንን የተለያዩ 10 ጋይድላይኖች በማስጫን ስራው ተከናውኗል።

ግብ **14**፡ የሴክተር አሰራር ስርዓቶችን በተሟላ መልኩ መዘርጋትና በቀጣይነት ማሻሻል፣

- በዓመቱ ውስጥ የሥጋ ምርመራና ህይጂን 10 ጋይድላይኖችን በማሻሻል ለማሳተም ከአለም አቀፉ የምግብና የእርሻ ድርጅት ጋር በመተባበር በመስራት ላይ የምንገኝ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የእንስሳት ጤና፣ ደህንነትና ቬትሪናሪ ፐብሊክ ሄልዝ አዋጅ ባለመጽደቁ ምክያንት የማሻሻል ስራው ከአዋጁ ጋር እንዳይጋጭና እንዲናበብ ለማድረግ ያስችል ዘንድ አዋጁ ይቅደም የሚል ሃሳብ ቀርቦ በመቀበል ለግዜው አዋጁ እስኪወጣ በመተባበቅ ላይ እንገኛለን፣ ነገር ግን 8 ጋይድላይኖችን የመከለስ ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን የማሳተሙ ስራ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል።
- በዓመቱ የሥጋ ምርመራና ህይጂን ደንብ በማርቀቅ ለዘርፉ ለማቅረብ ታቅዶ በሂደት (70 በመቶ) ላይ ያለ ሲሆን ለመዘግየቱም ምክንያት የዋናው ዓዋጅ ማለትም የእንሰሳት ጤና ደህንነትና ቬትሪናሪ ፐብሊክ ሄልዝ አዋጅ ሥራ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ነው። በቀጣይ ሩብ ዓመት ይጠናቀቃል።
- በዓመቱ 300 ጥራዝ የዓለም አቀፍ የጤና ሰርተፊኬት ለማሳተምና ለማሰራጨት የታቀዶ ተከናውኗል።
- በዓመቱ 5 ልዩ ልዩ የዕርድ መስመር ኤስ ኦ ፒ ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 የተከናወነ ሲሆን በዚህም ረገድ የባራኪ፣ የገፋፊ፣ የአንጀት አውጪ እና የኦርጋኒክ አሲድ ርጭት ኤስ ኦ ፒዎች ተዘጋጅተው ከቄራው ማናጅመንት ጋር በጋራ ወደ ስራ በማስገባት ጥቅም ላይ በማዋል የሥጋ ጥራትና ደህንነት ከፍ የተደረገ ሲሆን በቀጣይም ቀሪው የሚከናወን ይሆናል።
- በዓመቱ በዳይሬክቶሬታችን የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫ መስጫ መስፈርትን በማሻሻል ለበላይ አካል ለማቅረብ ቢታቀድም በንግድ ሚኒስቴር ከዚህ በፊት የምንጠቀምባቸውን የብቃት መስጫ መደቦች

እንደግብርና ሚኒስቴር ወደ 5 በማውረድ ብዙውን መደቦች በ 1 ያጠቃለለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያልተሰራ ቢሆንም በተለይ እንደ ቁም እንሰሳት መላክ፣ ተረፈ ሥጋ መላክ (ቀንድ፣ ሸሆና፣ ሰም፣ ጥሬ ቆዳ፣ ሌሎችንም) በአንድ የብቃት መስጫ መደብ የተጠቃለሉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከኳራንቲን ዳይሬክቶሬት ጋር በቀጣይ ተነጋግረን የሚሰራ ይሆናል።

- በዓመቱ በኤክ/ቄራ ለሚሰጡ የምርመራና ሰርተፊኬሽን አግልግሎቶች የሚከፈለውን ገንዘብ የአከፋፈል መመሪያ በማሻሻል ለበላይ ለማቅረብ ቢታቀድም ከስራው ስፋትና የኳራንቲንም አገልግሎት ክፍያ ጋር አብሮ መሰራት እንዳለበት ከዘርፉ አቅጣጫ በመሰጠቱ ምክንያትና በዳይሬክቶሬቱ አቅም ሊሰራ እንደማይችል የታመነ በመሆኑ በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንሲ በኩል እንዲሰራልን በዘርፉ በኩል ደብዳቤ የተጻፈ ስለሆነ በጋራ በቀጣይ የሚሰራ ይሆናል።

ዕይታ፣ መማማርና ዕድገት፣

ግብ **16.** የአመራርና ፈፃሚ እወቀት፣ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ፣

- በዓመቱ ለ 14 አዲስ ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ ሥልጠና ለመሰጠት ታቅዶ ሥለ ስጋ ምርመራና ሰርተፊኬሽን እንዲሁም ሃይጅንና ሳኒቴሽን ዙሪያ 12 ባለሞያዎችን ስልጠና በመስጠት የዕቅዱን 85.7 በመቶ አከናውኗል። ከዚህም በተጨማሪ ለባለሞዎቹ እንዴት በኤክስፖርቄራ ውስጥ ሥራቸውን በኃላፊነት መስራት እንደሚችሉ የግማሽ ቀን የሥራ ማስጀመሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሲቀጠሩ ተሰጥቷል።
- በዓመቱ ለነባር ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የተሀድሶ ሥልጠናው ለመሰጠት ታቅዶ ለ 55 ባለሞያዎች (91.7 በመቶ) በሀርድ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ተሰጥቷል።
- በዓመቱ ለነባር ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የ 6 ወራት የሥጋ ምርመራ ሥልጠና በሀርድ ፕሮጅክት ለመሰጠት ቢታቀድም ከስራ መደራረብ ምክንያት ፕሮፖዛሉ ባለመድረሱ ሳይከናወን ቢቀርም በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል።
- በዓመቱ በሞያ ስነምግባርና ስለ ጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ፋይዳ እንዲሁም ስለሚያስከትለው ጉዳት ለባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ከጸረ ሙስናና ስነምግባር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ለ59 ባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናውን በመስጠት የዕቅዱን 98.3 በመቶ ለማከናወን ተችሏል።

ግብ **18.** በቢሮ ያሉ ሥራ ከባቢዎችን ምቹ ማድረግ፣

- በዓመቱ በቢሮ ውስጥ የሚገኙ አላስፈላጊ የተበላሹ ዕቃዎችንና የተከማቹ ወረቀቶችን በአንድ ዙር ለማስወገድ ታቅዶ ለካይዘን አሰራር እንዲያመች ተደርጎ የተከናውነ ቢሆንም አሰራር ችግር በቢሮ ማስዋብ መጠገን ምክንያት አሁንም ወደ ሌላ ቢሮ የገባን ሲሆን ለሥራ የማይመችና ፓርቲሽን የሚያስፈልገው በመሆኑ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር በተደጋጋሚ በመነጋገርና የመፍትሄ ሀሳብ በማምጣት የተባሉትን ችግሮች በመቅረፍ የድርሻውን ተወጥቷል።

ከዕቅድ ውጪ የተሰሩ ሥራዎች፣

- በዳይሬክቶሬታችን እና በኳራንቲን ዳይሬክቶሬት የሥጋ መርማሪ ባለሞያዎችና የኳራንቲን ባለሞያዎች ለ2012 በጀት ዓመት የጥቅማጥቅም ፓኬጅ እንደ ኮሚቴ በመስራት ለበላይ ዓመራሩ ቀርቧል።

- ከሀምሌ 2010 እስከ ጥቅምት 2011 የትርፍ ሰዓት ክፍያ በበላይ ዓመራሩ ተይዞ እንዲከፈል በተግባባነው መሰረት ከዳይሬክቶሬቱ የሚጠበቀውን ማስረጃ የሰጠን ሲሆን በመጀመሪያው ዙር በቅርብ ለሚገኙ

ባለሞያዎች ከ 3 መቶ ሺህ ብር ያላነሰ የተከፈለ እና ሪፖርቱም የቀረበ ሲሆን ሁለተኛ ዙር ማጠቃለያ ክፍያም ቢዘገይም በበላይ ዓመራር በማስወሰን ክፍው ተከፍሏል።

- የጅግጅጋ እና የአበርገሌ ኤክ/ቄራዎችን ሥራ ለማስጀመር ያስችል ዘንድ ከድርጅቶቹ ማናጅመንትና ከኢንስፔክሽ ቡድኑ እና ከሥጋና ወተት ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ ሥራዎች ተሰርተዋል።

- ከዚህ ከሥጋ መርማሪ ሐኪሞችና ረዳት ሐኪሞች ቅጥር ጋር በተያያዘ ከሰው ሀብት ልማት ክሊራንስ ላመጡና የቅጥር ፎርማሊቲ ላሟሉ 12 ባለሞያዎች ዕጣ በማስወጣት በጅግጅጋ፣ በአዳሚ ቱሉ እና በመታህራ ኤክ/ቄራዎች በመመደብና ኦሪኤንቴሽን በመስጠት ሥራውንም በማስተዋወቅ ወደ ተመደቡበት ቦታ ሄደው ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል።

- ለ 11 ኤክስፖርት ቄራዎች እ.ኤ.አ የ2020 ዓመታዊ የሥራ ፍቃድ ዕድሳት"**Renewal of Certificate of Approval for Export Slaughter House"** ሰርተፊኬት በመስጠትና በተቀባይ አገሮች በማስመዝገብ ኤክስፖርቱ እንዲቀጥል ተደርጓል።
- ለ 4 አዲስ ኦፋል ላኪዎች ከተለያዩ ኤክስፖርት ቄራዎች ጋር ባደረጉት የውል ስምምነት መሰረት የንግድ ፈቃድ አውጥተው እንዲሰሩ በመስፈርቱ መሰረት በመገምገም ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል።

- ቤን ሮኢ ሥጋ ፋብሪካ በመባል የሚታወቀው በአዋሽ መልካሳ የሚገኘን አዲስ ኤክ/ቄራ የሳውዲ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን መጥተው በመጎብኘት ዕውቅና እንዲሰጡና የሥጋ ምርቱንም መላክ እንዲችል የግብዣ ደብዳቤ በማዘጋጀትና በዘርፉ በማስፈረም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የተላከ ሲሆን መልሱንም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

- ለሀርድ ፕሮጀክት ሥራ ማስኬጃ የሚውሉ የመኪና፣ የሞተር ሳይክል እንዲሁም የተለያዩ የቅዝቃዜ አመንጪ መሳሪያዎች ግዢ እና የአገልግሎት ግዢ (ኮንሱልታንሲ) ላይ በተዋቀረው ኮሚቴ ድምጽ ሰጪ አባል በመሆን በዘርፉ የተመደብን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጨረታውን የተሳተፉ 16 የሚደርሱ ተጫራቾችን ሰነድ (ቴክኒካል እና ፋይናንሺያል) በአውሮፓ ዩኒየን ህግ መሰረት በመገምገም አጠቃላይ ሪፖርቱን ለሚመከከተው ፕሮጀክት ቀርቧል።

- በ 33 ተኛው የእንሰሳት ሐኪሞች ማህበር ጉባዔ ላይ በመገኘት **"Opportunities and Challenges for Live animals and Meat Export Trade"** በሚል ርዕስ ወቅታዊ የአገራችንን የቁም እንስሳ እና የሥጋ ኤክስፖርትን በተመለከተ ያለበትን ሁኔታ የሚዳስስና የወደፊቱም ዕድሎችና ተግዳሮቶችን እንዲሁም ኤክስፖርን ለማሳደግ ምን ምን ነገሮች መሰራትና መሟላት እንደሚገባቸው የሚጠቁም አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ በማዘጋጀትና በኮንፈረንሱ ላይ በማቅረብ ከፍተኛ ውይይት ተካሂዶ ሁሉም በየቦታውና በተለያ የኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ የአገራችን የእንሰሳት ሐኪሞች የጋራ እንዲያደርጉትና እንዲደግፉት ለማድረግ ተችሏል።

- ለሶስት በዚህ በዕርድና በስጋ ኤክስፖርት ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች (2 ኢትዮጵያውያን እና አንድ የውጪ ዜጋ) በዘርፉ ስላለው ዕድል፣ ስጋቶችና ተግዳሮቶች እንዲሁም እንዴት ችግሮችን መወጣት እንደሚቻል በውይይት ምክርና ግንዛቤ የተሰጣቸው ሲሆን የሥጋ ንግድ እሴት ሰንሰለትን በተመለከተ እንደዚሁ ማብረሪ በመስጠት በንዑስ ዘርፉ ንግድ ውስጥ ቢሳተፉ የተለያዩ የኢንቨስትምንት ድጋፍ እንደሚደረግላቸው በተጨማሪ በማብራራት ኢንቨስትመንቱን ለመሳብ ተሞክሯል።

- በሞጆ ከተማ የሚገኘው የ FW Agro-production processing PLc የተባለ የዶሮ ቄራ የሥጋ ምርቱን ወደ ጅቡቲ ሪፑብሊክ ለመላክ ዝግጅቱን ያጠናቀቀእና በዳይሬክቶሬታችን ተገምግሞ ፈቃድ እንዲሰጠው በጠየቀው መሰረት በቄራው በመገኘት የኦዲትና የኢንስፔክሽን ሥራዎችን በመስራት ቄራው በጥሩ የአመራረት ሥርዓት ውስጥ ያለ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ነገር ግን መስተካከል የሚገባቸውን አንዳንድ ሂደቶችን በኦዲት ግኝት ግብረ መልስ የተሰጠ እና የተስተካከለ መሆኑን በማረጋገጥ በዘርፍ ደረጃ የጅቡቲ ሪፑብሊክ የተቆጣጣሪ ሀኪሞች ቡድን እንዲመጡና ቄራውን እንዲዩት በደብዳቤ በመጋበዝ የመጡና ያዩት እንዲሁም ዕውቅና የሰጡት በመሆኑ የሥጋ ምርቱን በቅርቡ መላክ የሚጀምር ይሆናል።

- የአቢሲኒያ ኤክ/ቄራ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ወደ ሳውዲ የተላከ አንድ ባች ምርታቸው ልብሊንግ ላይ ኦርጋኒክ በሚል ምክንያት የተያዘባቸውና የግብርና ሚኒስቴር የሚመለከተው አካል ማብራሪያ በመስጠት ምርቱ ሊለቀቅ እንደሚችል በጠየቀው መሰረት በጉዳዩ ላይ በጥልቀት በመነጋገርና ማብራሪ ለሳውዲ አራቢያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን በመጻፍ ምርታቸውን ለማስለቀቅ ተችሏል። ለወደፊቱም ኦርጋኒክ ምርት መሆኑ በሳይንሳዊ ትንተና በ3 ተኛ አካል ሳይረጋገጥ እንዳይጻፍ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከምርት ሌብሊንጉ ላይ ከዚህ ግዜ ጀምሮ እንዲሰረዝ በማድግ ኤክስፖርቱ እንዲቀጥል ተደርጓል።

- የእንስሳት ሀብት ልማት እንቅስቃሴ ወቅቱ ከሚጠብቀው አንፃር ተቀናጅቶ መንቀሳቀስ እንዲቻል የመስክ ድጋፍ በጋራ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሱፐርቪዥን ቼክሊስት እንደ ዘርፍ በማዘጋጀት ወደ ሱማሌ ብ/ክልላዊ መንግስት የእንሰሳት ሀብትና አርብቶ አደር ልማት ቢሮ የወረዳ አካላት የራሱንና የአካባቢው ማነቆዎች በመለየት ለመፍታት የሚያስችል ዝግጁነት በመፍጠር ለዘርፉ እድገት እንዲተጉ ለማድረግ እንዲሁም በመስክ በመገኘት ሞያዊ ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ በማድረግ ወቅታዊ የሆነ የአፈጻጸም ደረጃ በመለየት ቀጣይ ለሚሰራ ስራዎች የዕቅድ አካል 4 ባለሞያዎች በመሆን ወደ ክልሉ በመንቀሳቀስ ያገዘን ሲሆን ይህንንም የመስክ የሥራ እንቅስቃሴ በተደራጀ መንገድ ለዘርፉ በመስክ መልስ ሪፖርት መሰረት አቅርበናል።
- የሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ እንደዓቅሙ በተለያዩ ምክንየቶች ሥራ መስራት ባለመቻሉ ምክንያት ሚ/ር መ/ቤቱ በኪራይ ውል ስምምነት ወይም በመንግስት-ግል አጋርነት መርህ (Publike Private Partnership Principle) ጣቢውን የማስተዳደር (ማናጅመንት) ሃላፊነት ለግል ባለሀብት ለመስጠት በወሰነው መሰረት ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመሆንየክፍተት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ለዘርፉና ለሚኒስትር ጽ/ቤት ሪፖርቱን በማቅረብ ለውሳኔያቸው ግብዓት ሰጥተናል።

ዋና ዋና ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትዎችና ሊወሰዱ ታሰቡ እርምጃዎች፣

- ከዚህ በፊት ማለትም 2010 እና ከዚያ በፊት ለዳይሬክቶሬቱ ይመደብ የነበረው የሞባይል ካርድ በመቋረጡ ምክንያት ከኤክ/ቄራዎች ጋር ከስራ ሰዓት ውጪ በተለይም ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በባዕላት ቀናት በመገናኘት ለመደገፍም ሆነ መረጃ ለመለዋወጥ አልተቻለም። በተደጋጋሚም ብናሳውቅም ሊስተካከል አልቻለም። ሆኖም በየኤክስፖርት ቄራ ያሉ አስተባባሪዎችና ዳይሬክተሩ ከደሞዛቸው በመቀነስ የሞባይል ካርድ በመግዛት የመንግስትን ስራ እየደገፉ የሚገኙ ሲሆን ሚ/ር መ/ቤቱ ይህንን የሥራ ጸባይ በማየት ከበፊቱም በተሻለ ሁኔታ ሞባይል ካርድ ምደባ በማድረግ ኤክስፖርቱ እንዲሳለጥ ቢያደርግ፣ ለሁሉም የቄራ ኢን/ሰርተ/አስተባባሪዎችም ታስቦበት የሚመደብበት ሁኔታ ቢመቻች። የጣቢያ አስተባባሪዎች የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ የኢቪዶዮ መሳሪያ ቢመደብላቸውና ሳምታዊ ሪፖርት በወቅቱ የሚላክበት ሁኔታ ቢመቻች፣

- በአልኑጁምና በሉና ኤክ/ቄራዎች የሰርቪስ መኪና የሌላቸውና በእግርና በባጃጅ እንደዚሁም ባለሀብቱን በማስቸገር ወደ ሥራ የመግባትና የመውጣትና ሁኔታዎች ላለፉት ዓመታት የታዩና ያልተቀረፉ ችግሮች

መሆናቸው በተደጋጋሚ የተነገረ እና በተጨማሪም ኤክ/ቁራዎቹ ከከተሞች ወጣ ብለው የተገነቡ በመሆኑ ችግሩን የከፋና ለኪሳራም የዳረጋቸው መሆኑ ባለሞዎች በምሬት ይገልጻሉ። በመሆኑም ክቡር ሚኒስትሩ ከዚህ በፊት በእንሰሳት ጤና እና ልማቱን ዘርፎችን ሲገመግሙ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት ሁሉም ቁራዎች የሠርቪስ መኪና እንዲመደብላቸው ቢደረግና ኤክስፖርቱ ቢሳለጥ፣ በተለይም ከ Livestock sector Development project ከተገኙ መኪኖች ወይንም ካሉ መኪኖች የሚመደብበት ሁኔታ ቢመቻች፣

- በቅርቡ በቢሮ ዕድሳት ምክንያት ወደ አዲስ ሚ/ር መ/ቤቱ ወደ ተከራየልን ባለ 3 ፎቅ ቢሮ መግባታችን የሚታወስ ሲሆን ይህ ቢሮ ግን የሚከተሉት መሰረታዊ ችግሮች የሚታዩበትና ካልተስተካከሉ በስተቀር የተሰጡንን ተልዕኮዎችና ተግባራት ለማከናወን የራሱ የሆነ ከፍተኛ ጫና የሚያስከትል መሆኑን በመግልጽ ያሉትች ችግሮች ከመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በከፍተኛ ችግር ውስጥም ሆነን ሥራችንንም እየሰራንም በላያችንም ላይ የማስተካከያው ሥራንም እየተሰራ የቆየን ሲሆን የዋናው ቢሮ ሥራእንዳለቀ በደ ነበርንበት ቢሮ እንድንመለስ ከወዲሁ እንዲታሰብበት ቢደረግ።

- የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት
- የ**2012** በጀት ዓመት የአራተኛ ሩብ ዓመትና አመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| ህብረተሰባዊ/ሃገራዊ 30 በመቶ | ግብ 1. የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | በዳይሬክቶሬቱ በተሠጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የረኩ ተገልጋዮች (ኤክስፖርት ቄራዎች) | የተገልጋይን የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አሁን ካለበት 80 በመቶ ወደ 90 ማሳደግ | የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | የተጠና ጥናት በቁጥር | 2 | - | 1 | 2 | 1 | 2 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | ጥናቱን በመተንነን ዕርካታን ወደ 90 ማድረስ | በመቶኛ | 95 | - | 95 | 95 | 90 | 90 | 90 | 90 | 90 | |
| | ግብ 2. የተገልጋይ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥጋ አመራረት ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸውና ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ተገልጋዮች | የኤክስፖርት ቄራ የዕርድ መስመር ሰራተኞችንና የቦሌ ስጋ አውራጅ-ጫኝ ሰራተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | በተለያዩ ኤክስፖርት ቄራዎች ለሚገኙ የዕርድ መስመር ሠራተኞች ስለ ዘመናዊ የእንሰሳት አስተራረድና አገፋፈፍ ሥርዓትና ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተሃድሶ ሥልጠና መስጠት፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 1000 | - | 300 | 1000 | 506 | 1250 | 168.7 | 125 | 125 | |
| | | | | ቦሌ አየር መንገድ ፍረሽ ፖርት ለሚገኙ የስጋ አውራጅ-ጫኝ ሰራተኞች ሥለ ሥጋ አያያዝና ደህንነት እንዲሁም የግል ንጽህና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት | የሠልጠኝ ብዛትበቁጥር | 50 | | 25 | 50 | - | 30 | - | - | 60 | |
| | ግብ 4. የእንሰሳትና አሳ | የተሻሻሎ ደህንነቱና ጥራቱ | ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ | የቅድመ ዕርድ ምርመራ ማካሄድ | በሺህ ቁጥር | 4134 | | 1133.5 | 4134 | 642.15 | 1856 | 56.7 | 44.9 | 44.9 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ግብአትና ምርት ጥራት ቁጥጥር ማሻሻል | ተጠብቆ የተመረተ ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣ | ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽን ና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መስጠት | ዳልጋ ከብት | `በሺ ቁጥር | 30 | | 7.5 | 30 | 6.5 | 27.71 | 86.7 | 92.4 | 92.4 | |
| | | | | በግና ፍየል | `በሺህ ቁጥር | 4104 | | 1126 | 4104 | 635.65. | 1828.29. | 56.5 | 44.5 | 44.5 | |
| | | | | የድህረ ዕርድ ምርመራ ማካሄድ | `በሺህ ቁጥር | 4130 | | 1132.5 | 4130 | 625.53 | 1799 | 55.2 | 43.6 | 43.6 | |
| | | | | ዳልጋ ከብት | `በሺህ ቁጥር | 30 | | 7.5 | 30 | 6.5 | 27.71 | 86.7 | 92.4 | 92.4 | |
| | | | | በግና ፍየል | `በሺህ ቁጥር | 4100 | | 1125 | 4100 | 619.03 | 1771.29 | 55.0 | 43.2 | 43.2 | |
| | | | | ምርመራ ተካሂዶበት ወደ ውጪ የተላከ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት | በቶን | 43000 | | 12500 | 43000 | 3619.92 | 14273 | 29 | 33.2 | 33.2 | |
| | | | | ምርመራ ተካሂዶበት የተላከ የሥጋ ምርት፣ | በቶን | 41000 | | 12000 | 41000 | 3319.88 | 12348 | 27.7 | 30.1 | 30.1 | |
| | | | | ዳልጋ ከብት ሥጋ | በቶን | 4000 | | 1000 | 4000 | 57 | 400.52 | 5.7 | 10 | 10 | |
| | | | | በግና ፍየል ሥጋ | በቶን | 37000 | | 11000 | 37000 | 3262.88 | 11947.48 | 29.7 | 32.3 | 32.3 | |
| | | | | ምርመራ ተካሂዶበት የተላከ የተረፈ ሥጋ ምርት | በቶን | 2000 | | 500 | 2000 | 300.4 | 1925 | 60.1 | 96.3 | 96.3 | |
| | | | | ለምርቶቹ የተሰጠ የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት | በቁጥር | 8000 | | 2300 | 8000 | 2449 | 8150 | 106.5 | 101.9 | 101.9 | |
| ሃብት (10 በመቶ) | ግብ 8. የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | | የዳይሬክቶሬቱን የበጀት አጠቃቀም | የበጀት አጠቃቀምን ከነበረበት 72 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ | በመቶኛ | 90 | - | 70 | 80 | 80 | 80 | - | 80 | 80 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | ውጤታማነትን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | |
| | ግብ 9. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | በተለያዩ ሥራዎች በመስራት የተገኘ ሀብት | የሃብት ግኝት ማሳደግ | በበጀት ዓመቱ ኤክ/ቁራዎች የአገልግሎት ክፍያ ወደ ባንክ አካውንት እንዲስገቡ ማድረግ፣ | በሚሊዮን ብር | 2.5 | | 0.7 | 2.5 | 0.346 | 1.1985 | 33.6 | 49.4 | 48 | |
| | | | | ሀብት ሊያስገኙ የሚችሉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ፕሮፖዛሎች በቁጥር | 1 | | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| የዉስጥ አሰራር (45 በመቶ) | ግብ 10. ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት | ተለይቶና ተቀምሮ የተስፋፋ ምርጥ ተሞክሮ፣ | በቁራዎች ሊገኝ የሚችልን ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት፣ | የተለየ ምርጥ ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | | - | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | የተቀመረ ምርጥ ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | | - | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | የተስፋፋ ምርጥ ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | ግብ 11. ቅንጃዊ አሰራርን ማሳደግ | ያደገና የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር | ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ | የሳውዲ እና የዱባይ የኢንስፔክሽን ቡድንን በመጥራት አዲስ ወደ ስራ የገቡ ቁራዎችን በማስገምገም ምርታቸውን እንዲልኩ ማስቻል፣ | ምርታቸውን ለመላክ የቻሉ ቁራዎች ብዛት | 2 | | - | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | ከእንሰሳት መድሃኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ጋር በመቀናጀት በስጋ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ጎጂ ቅሪትቶችን (Residues) በማመመርመር የላቦራቶሪ ውጤት ማውጣትና ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፣ | የወጣ የላቦራቶሪ ወጤት በሰነድ | 2 | | 1 | 2 | - | 0.5 | - | 25 | 25 | |
| | | | | ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/፣ ከሥጋ አምራች ላኪዎች ማህበር፣ ከመ/ቤታችን የገበያና ግብይት ዘርፍ ቅንጅታዊ ጥምረት በመፍጠር የሥጋ ምርመራና ኤክስፖርት ሥራዎችን ማሳለጥ፣ | የተፈጠረ ቅንጅታዊ ትስስር የተራ ሥራ ብዛት | 4 | | 1 | 4 | 1 | 5 | 100 | 125 | 125 | |
| | | | | የብሔራዊ የኤስ ፒ ኤስ ኮሚቴን ሥራዎችን በማስተባበር ምክረ ሀሳብ ለበላይ ዓመራር ማቅረብ፣ | የቀረበ ምክረ ሀሳብ | 4 | | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |

| ዕ ይ ታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ግብ 12. የክትትል ግምገማና ድጋፍ ስርአትን ማጠናከር | ወቅታዊ ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ተደርጎለት የተጠናከረ የኢንስፔክሽን ና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት፣ | በሥርዓት ላይ የተመሰረተ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መገንባት፣ | ኤክስፖርት ቄራዎች በሚኒስትር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ስታንዳርድ የአሰራር ሥርዓት (SOP) እና በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000) ሥርዓት መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ማድረግ፣ | በክትትልና ቁጥጥር ግዜ | 4 | | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000-2017/18) ወይም ሃስፕ (HACCP) ሥርዓት በሶስተኛ አካል ዕውቅና ያገኙና በዳይሬክቶሬታችንም ተገምግመው ይሁንታን አግኝተው በትክክል በስርዓቱ መሰረት እየተገበሩ ያሉ ቄራዎች፣ | ኤክ/ቄራ ዎች ብዛት | 12 | | - | 12 | - | 10 | - | 83.3 | 83.3 | |
| | | | | የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ፣ | የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር፣ | 4 | | 1 | 4 | 1 | 3 | 100 | 75 | 75 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | የአዳዲስ የኤክስፖርት ቁራዎች እና የሥጋ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ግንባታ ክንውን በመመሪያና ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ከቦታ መረጣ ጀምሮ መከታተል እና መቆጣጠር | በክትትል ግዜ | 4 | | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | ኤክስፖርት ቁራዎች የሚገኙትን አነስተኛ ላቦራቶሪዎች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ | ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው የቁራ ላቦራቶሪዎች ብዛት | 11 | | 6 | 11 | 3 | 10 | 50 | 90.1 | 90.1 | |
| | | | | አሁን እየላክን ካሉት አገራት በተጨማሪ ሌሎች አዲስ አገራት ለመላክ የሚያስችል ስምምነት በማድረግ የወጪ ገበያን ማስፋፋት፣ | የተጨመሩ አዲስ አገሮች በቁጥር | 1 | | - | 1 | | 0.5 | - | 50 | 50 | |
| | | | | የጅግጅጋን ኤክ/ቁራን ያለበትን ችግር ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና በመፍታት ኤክስፖርት እንዲጀምር ማድረግ፡ | ኤክስፖርት የጀመረ ቁራ | 1 | | - | 1 | - | 0.6 | - | 60 | 60 | |

| ዐይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ግብ 13.የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽን ማጎልበት | የጎለበተ የመረጃአቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽን | የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽንን ማጎልበት | የኤክስፖርት ቄራዎችን ሳምንታዊ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ማቀናጀት | ተሰብስበው የተቀናጁ ሪፖርቶች በዛት | 200 | | 50 | 200 | 43 | 191 | 86 | 95.5 | 95.5 | |
| | | | | የኤክስፖርት ቄራ አገልግሎት ወርሃዊ የበሽታ ግኝት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ማደራጀትና መተንተን እና ማሰራጨት | ተሰብስቦ የተደራጀ እና የተሰራጨ መረጃ | 2 | | 1 | 2 | 1 | 2 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | በሚ/ር መ/ቤታችን ዌብ ሳይት አስፈላጊ መረጃዎችን በመጫን ለተገልጋዩ ተደራሽ ማድረግ | የተጫኑ መረጃዎች ብዛት | 10 | | - | 10 | - | 10 | - | 100 | 100 | |
| | ግብ 14፡ የሴክተር አሰራር ስርዓቶችን በተሟላ መልኩ መዘርጋትና በቀጣይነት ማሻሻል | በተሟላ መልኩ የተዘረጉና በቀጣይነት የሚሻሻሉ የሴክተር አሰራር ስርዓቶች፣ | የዳይሬክቶሬቱን የአሰራር ስርአቶች ውጤታማነት ማሳደግ | የሥጋ ምርመራና ሀይጂን ጋይድ ላይን በማሻሻል ማሳተም | ተሻሽሎ የተዘጋጀ ጋይድ ላይን | 10 | | - | 10 | 8 | 8 | | 80 | 80 | |
| | | | | የሥጋ ምርመራና ሀይጂን ደንብ በማርቀቅ ለዘርፉ ማቅረብ | የቀረበ ደንብ | 1 | | - | 1 | - | 0.7 | - | 0.7 | 0.7 | |
| | | | | የዓለም አቀፍ የጤና ሰርተፊኬት ማሳተምና ማሰራጨት | ጥራዝ ብዛት | 300 | | 300 | 300 | 200 | 300 | - | 100 | 100 | |
| | | | | ልዩ ልዩ የዕርድ መስመር ኤስ ኦ ፒ ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ኤስ ኢፒ ብዛት | 5 | | 3 | 5 | 2 | 4 | - | 80 | 80 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | የብቃት ማረጋገጫ መስጫ መስፈርትን በማሻሻል ለበላይ አካል ማቅረብ | የቀረበ ሰነድ | 1 | | | 1 | - | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | በኤክ/ቄራ ለሚሰጡ የምርመራና ሰርተፊኬሽን አግልግሎቶች የሚከፈለውን ገንዘብ የአከፋፈል መመሪያ በማሻሻል ለበላይ ማቅረብ | የቀረበ መመሪያ | 1 | | | 1 | 0 | 0 | 0 | 0- | 0 | |
| መማማርና እድገት (15%) | ግብ 16 የአመራርና ፈፃሚ እወቀት፣ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ | እወቀቱ፣ክህሎትና አመለካከቱ ያደገ ኣመራርና ፈጻሚ | የአመራር እና ፈጻሚ ክህሎት እና አመለካከትን ማሳደግ፣ | ለአዲስ ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መሰጠት ፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 14 | | - | 14 | - | 12 | | 85.7 | 85.7 | |
| | | | | ለነባር ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የተሀድሶ ሥልጠናው መሰጠት ማድረግ፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 60 | | 60 | 60 | - | 55 | - | 91.7 | 91.7 | |
| | | | | ለላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች ስለ ላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች ከሰበታ ላቦራቶሪ ጋር በመተባበር የተሀድሶ ሥልጠናው እንዲሰጣቸው ማድረግ፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 10 | | 10 | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | ለነባር ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የ 6 ወራት የሥጋ ምርመራ ሥልጠና በሀርድ ፕሮጅክት መሰጠት፣ | የሠልጠኝ ብዛትበቁጥር | 25 | | - | 25 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | በሞያ ስነምግባርና ስለ ጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ፋይዳ ለባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት፣ | የባለሞያ ብዛት | 60 | | | 60 | - | 59 | - | 98.3 | 98.3 | |
| | ግብ. 17. የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት አጠቃቀም አቅም ማሳደግ፣ | አቅርቦቱና የአጠቃቀም አቅሙ ያደገ የኢንፎርሜሽንኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ | የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት አጠቃቀም አቅም ማሳደግ፣ | ለ10 ኤክስፖርት ቄራዎች ደስክ ቶፕ ኮምፑተር፣ ፕሪንተርና ላብቶፕ በመግዛት ማሰራጨት፣ | ተገዝቶ የተሰራጨ ብዛት | 20 | | 20 | 20 | 5 | 5 | 20 | 20 | 20 | |
| | ግብ 18. ለስራምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ማሻሻል፣ | የተሻሻሉና ለሥራ ምቹ የሆኑ ከባቢያዊ ሁኔታ፣ | በቢሮ ያለ ሥራ ከባቢዎችን ምቹ ማድረግ፣ | በቢሮ ውስጥ የሚገኙ አላስፈላጊ የተበላሹ ዕቃዎችንና የተከማቹ ወረቀቶችን ማስወገድ፣ | በ 2 ዙር የተወገዱ የተበላሹ ዕቃዎችና ወረቀቶች | 2 | | | 2 | 1 | 3 | - | 150 | 150 | |